በያህሹዓ የሆነ የያህዌ ጉባኤ(YAIY) የእምነት ዐንቀጽ

የዕምነት መሠረት

መግብያ

ይህን ሰነድ እንደ እምነት መሰረት አድርጎ ያዘጋጁት በመስሒ ያመኑት ወንድሞች ሲሆን ይህም እምነት አንድ ግዜ ለቅዱሳን የተሰጠ ነው ( ይሁዳ 1:3)። ከዝህ በታች የተነሱት ዋና ዋና ሐሳቦች ለኛ እምነት መሰረት የሚሆኑ ናቸው፤ ስለዚህ በቶሎ እንድታነቡት እንመክራቸዋለን። ሁሉንም ፈትኑ መልካሙን ያዙ (1ተሰሎንቄ 5፡21)። ያስቀመጥነው የእምነት ትምህርት እምነታችንን እንደ አጠቃላይ የሚገልጽ እና ሁላችንም የምናምንበት አስተምህሮ ነው።

ከዝህ በታች የተዘረዘሩትን እውነታዎች ያስቀመጥናቸው በእውነተኛው የያህዌ ቃል ለይ በመመስረት ነው።

1.መጽሐፍ ቅዱስ(THE BIBLE)

መጽሐፍ ቅዱስ በያህዌህ መንፈስ መሪነት የተጻፈ እና የሰው ልጅ በራሱ መማር የማይችል ዕዉቀት ነው። ከያህዌ አፍ በምወጣው በእያንዳነዱ ቃል መኖር አለብን(ማቴ4፡4)።

‹‹የያህዌ መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለዉ ምክር ደግሞ ይጠቅማል (2ጢሞ3፡14-16)። መጽሐፍ ቅዱስ(ትንቢት) የያህዌህ ቃል እንጂ በሰው ፍቀድ የመጣ አይደለም(2ጴጥ1፡21)። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ አይቻልም(ዘዳግም4፡2፣12፡32፤ምሳ30:6፣ራእይ22፡18 ተመልከት) ።

2.አብ(አባት)(THE FATHER)

አብ ብቸኛ የፍጥረት ሁሉ ምንጭ፣ዋና አዘጋጅ፣የሁሉም አስገኚና ፈጣሪ ነው። ፍጥረትንም ሁሉ የፈጠረው በልጁ በኩል ነው(ምሳሌ8፡22-31፣ ራእይ3፡14 ፣ቆላ1፡15-17፣ዮሐ1:3)። በመጀመሪያ(ኦሪጂናል)መጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው የሰማይ አባታችን ስም ያህዌህ[יהוה]ተብሎ ነው(ዘጸ3፡13-15፣መዝ22፡22፣68፡4፣ኢሳ42፡8፣ኤር16፡21፣ዮሐንስ17፡11፣ኤፌ3፡14 -15) ተመልከት።ስሙም ለዘለዓለም ያህዌህ[יהוה]ተብሎ ይታወቃል። (ዘጸ3:13-15;ኢሳ63:12፣66:5;ሚል4:5;ዘከ4:9) አብ የሁሉ ስልጣናትና ሀይላት ምንጭ ስለሆነ ሁሉም ምስጋናና አምልኮ ለእረርሱ ብቻ ይገባዋል።

ማቴ4፡10፣6፡9 ፣ቆላ1፡12 ፣ያዕ1፡17፣1ጴጥ2፡5፣ፊል2:11፣ቆላ3:17 ተመልከት። ሁሉም ስግደትና ኣምልኮ ለእረሱ የሚቀርበው በልጁ በያህሹዓ መስሒ በኩል ነው። ዮሐ14፡6፣ኤፌ5፡20፣ፊል2:11፣ቆላ3:17 ተመልከት።

ያህዌ መንፈስ ነው(ዮሐ4፡24)

ያህዌህ የያህሹዓ መሲሕ አምላክና አባት ነው(2ቆሮ1:3፣ኤፌ1:3፣17)

3.ወልድ(ልጅ)(THE SON)

ትክክለኛ የጌታችንና የመድሐንታችን ስም ያህሹዓ ተብሎ ይታወቃል። ይህም ስም "ያህዌ"እና"ሆሹዓ"በውስጡ የያዘ ስሆን ትርጉሙም "የያህዌ መዳን"ወይም"ያህዌ መዳኒት ነው"የሚል ፍች ይሰጣል።ምክንያቱም እንድንበት ዘንድ ያህዌ ለሰው ልጅ ያዘጋጀው ስም ያህሹዓ የሚል ብቻ ነው።

(ማቴ1:21፣ሉቃ2:31፣ዮሐ3:16፣ሐዋ4፡12)።

ያህሹዓ ቃል[דבר]ነበረ ፣ከመወለዱ በፊትም በአባቱ በያህዌ ዘንድ ነበር(ዘፍ1፡26፣ዮሐ1፡1-3፣ዮሐ8፡58፣ዮሐ13፡3፣1ቆሮ10፡4፣ቆላ1፡15-17)።እርሱ የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ (ፍል2፡5-7፣ዮሐ17፡5፣ዕብ2፡6-14)።

እርሱ ከድንግል ሴት በያህዌ ሀይል የተወለደ(ኢሳ7፡14፣9፡6፣ማቴ1፡18፣1፡23፣ሉቃስ1፡26-38)፣ በአባቱ በያህዌ ስም የመጣ(ዮሐ5፡43)፣ምንም ሃጥያት ያልሠራ(ኢሳ53፡9፣1ጴጥ2፡22)፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል በሶስተኛዉ ቀን ከሙታን የተነሳ(ማቴ12፡20፣ሐዋ3፡15፣1ቆሮ15፡3-4)፣ ወደላይ ወጥቶ በያህዌ ቀኝ የተቀመጠ(ማር16፡19፣ሉቃ24፡51፣ዕብ1፡13)፣ጠበቃችን (1ዮሓ2፡1)፣መካከለኛ(1ጢሞ2፡5)እና ልቀ ካህን ነው(ዕብ3፡1፣4፡14)።በአጠቃላይ ወደ ሰማይ አባታችን ልንቀርብ የምንችለው በእርሱ በኩል ብቻ ነው(ዮሐ14፡6)።

4.መንፈስ ቅዱስ(THE HOLY SPRIT)

መንፈስ ቅዱስ ሰዉ አይደለም ስለዚህ ስጋና አጥንት የለዉም(ሉቃስ24፡39)፤በንፋስም ተመስሏል(ሉቃ24፡49፣ዮሐ3፡8፣ሐዋ10፡45፣2፡2)።ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ትልቅ የማይታይ ፣ከአብ የሚወጣ እና በልጅ በኩል ለአማኞች የሚሰጥ ሀይል ነው(ዮሐ14፡26፣15፡26 ፣ሐዋ2፡33፣1ቆሮ2፡10-16፣ቲቶ3፡6)። አማኝ በያህሹዓ መሲሕ ስም ከተጠመቀ በኃላ፤ በሽማግሌዎች እጅ መጫንም መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል(ሐዋ8፡17፣19፡6፣1ጢሞ4፡14፣2ጢሞ1፡6፣ሐዋ5፡32)። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመስሒ አካል ጋር አንድ ያደርገናል(ሮሜ8፡15-17፣1ቆሮ12፡13፣ገላ3፡28)። ያህሹዓንና አብን መውደዳችን የምንገልጸው በተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ሀይል ህጉን ከጠበቅን ብቻ ነው(ዮሐ14፡15፣ዮሐ14፡21-24፣ሐዋ1፡8፣1ዮሐ2፡5)።5.ጥምቀት(BAPTISM)

ጥምቀት ከእውነተኛ ንስሐ መግባት ቦኃላ፣በያህሹዓ መሲሕ ስም ውሃ ውስጥ በመጥለቅ፤የሚደረግ የኃጥያት ማስተሰረያ ነው(ሐዋርያት2፡38፣ሐዋርያት4፡12፣ሐዋርያት8፡16፣ሐዋርያት10፡43-48፣ሐዋርያት19፡5፣ሮሜ6፡3፣ሉቃስ24፡47፣ማርቆስ16፡15)። መዳን ከያህሹዓ መሲሕ ስም በቀር በሌላ በማንም የለምና(ሐዋ4፡12)። አንድ ግዜ ወደ ኃላ ውሃ ውስጥ መጥለቅችን፣ አሮጌውን ሰው በመቀበር እና ሞቱን በሚመስል ሞት መተባበራችንን ያመለክታል(ሮሜ6፡3-5፣ቆላ2፡12)። እንድሁም ከውሃ ስንወጣ በአዲስ ህይወት መመላለስን(መገልገልን) ያመለክታል(ሮሜ7፡6፣12፡1፣1ጴጥ3፡21)። አማኞችን አንድ አካል የሚያደርግ በመድሐኒታችን በያህሹዓ መሲሕ ስም የሚደረግ አንድ ጥምቀት ብቻ አለ(ሮሜ12፡5፣ኤፌ4፡3-6፣1ቆሮ12፡12-14)

6.ሕግ(LAW)

ያህዌ ለሰው ልጆች ያዘጋጀው ብቻኛ የማዳን መንገድ በልጁ በያህሹዓ መስሒ በኩል ስሆን ይህም የሚገለጸው የያህዌን ሕግ(ትዕዛዛት) በመጠበቅ ነው። በያህሹዓ መሲሕ የሚደረግ የመዳን መንገድ በተለያየ እንስሳት ይደረግ የነበረዉ የመስዋዕቱ ደምና የሁል ግዜ የቤተመቅደስ ስርዓት የያህዌ በግ በሆነው በያህሹዓ መሲሕ ፍጻሜ በማግኘቱ ነዉ (ሌዊ231፣ዘኍ28-29፣ዮሐ1፡29፣ዕብ.ም8-10)። አሁን መስወዕታችን መንፈሳዊ ነው(ሮሜ12፡1 ዕብ13፡15-16፣1ጴጥ2፡5)። መገረዝ ማለት ሁል ጊዜ በፈቃደኝነት ከልብ መታዘዝ(የልብ ግርዘት)ማለት ነው(ዘዳ10፡16፣30፡6-8፣ኤር4፡4፣1ቆሮ7፡19፣ገላ5፡6፣ፍል3፡3)። አሁን በያህሹዓ በማመን ፣ውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ መሪነት ትእዛዛቱን መጠበቅ ይቻላል (ሕዝ36:27፣ዘዳ7፡9፣ መዝ119፡160፣ማቴ5፡17-19፣19፡16-19፣ኤፌ2፡8-10፣1ዮሐ1፡1-5፣1ዮሐ3፡21-24 ተመልከት)።

7.ሰንበት (SABBATH)

ከሳምንቱ ሰባተኛው ቀን(ቅዳሜ) ያህዌህ የለየ እና ሁሉን ቻይ የሆነው የመፍጠር ኃይሉ መታሰቢያ ነው(ዘፍ2፡2-3)። የሰንበት ቀን የተቀደሰ የዕረፍት ቀን ነው(ዘጻ20፡8-11)። የሰንበት እረፍት ምሳሌ የምመጣውን የአንድ ሺህ ዓመት ዕረፍትን ያመለክታል(ዕብ41-11 ፣ማቴ11፡28-30)።የሰንበት ዕረፍት ለያህዌ ያለን ፍቅር፣ ታማኝነት እና ቁርጠኝነት የምንገልጽበት ምልክትም ነው፣(ዘጻ31፡13)። ያህዌ የሰንበትን ቀን የሰጠን የሰራውን ድንቅ ፍጥረታትንና ቤዛነቱን እንድንመሰክር ነዉ (ማር2፡27-28፣ ዕብ4፡7-11)። የሰንበት ተካፋይ በመሆን ያህሹዓ እንደ ፈጣሪ(በሱ በኩል)እንድሁም የመዳናችን ጀማሪና ፈጻሚ እንደሆነ እናምናለን(ዕብ12፡2)። ለእረፍታችን እና ለአምልኳችን የወሰነውን ግዜ በመቀደስ፣ ለፊቃዱ መገዛታችንን እናሳያለን፣ እናም በህይወታችን እና በፍጥረት ሁሉ ላይ የእርሱን ገዥነት እንገነዘባለን። "የሰንበት እረፈት አሁንም ለያህዌ ህዝብ ቀርቶላችዋል"(ዕብ4፡9)። የሰንበት ቀን የደስታ ቀን እንጂ የስራ ቀን አይደለም (ኢሳያስ 58፡13)።

8.የፋስካ ሰንበት (PASSOVER)

የሞት መልአክ በ14ኛው ቀን እኩለ ሌሊት ላይ በመጣበት በግብፅ በነበረው የፋሲካ ሰንበት መሠረት፣ የያህሹዓ መሲሕ ውድ መሥዋዕት መታሰቢያም በየዓመቱ በአቢብ 14ኛው ምሽት (መጀመሪያ ላይ)ማለትም በ13ኛው ማብቂያ ላይ ይከበራል(ዘጸ12፡13-14)።በትህትና የፋሲካን ሰንበት ስንካፈል፣ ስለ ኃጢአታችን የፈሰሰውን የመሲሕ ደም እንደምንቀበል እንመሰክራለን (ዘኍ28፡16፣ ሉቃ22፡15-20፣1ቆሮ11፡23-29)። የተወጋ ስጋውን የሚወክል እርሾ የለለው ቂጣ መብላት(ዘጸ23፡18፤1ቆሮ10፡16)፣ እና የፈሰሰው የደሙን የሚወክል የወይኑ ጭማቂ፣ መጠጣት፣ በረሱ በያህሹዓ የተቋቋሙ ስርዓቶች ናቸው(ዘዳ32፡14፣ኢሳ65፡8-9፣ማቴ26፡27-29)። ለያህሹዓ ያለን ፍቅርና በወንድሞች መካከል ያለውን ትህትና ሚያሳይ እግር መተታጠብም፣በጌታችንና በመደሀኒታችን የተዘዝን ስነስርዓት ነው(ዮሐ13፡3-17)።

9.የቂጣ ሰንበት(FEAST OF UNLEAVENED BREAD)

ፋሲካ ከበላን በኋላ የሚቀጥሉትን ሰባት ቀናት የቅጣ ሰንበት ስናከብር ከኃጢአት የጸዳ፤ የታዛዥነት ሕይወት ለመኖር እንጥራለን(ሌዊ23፡6፣ ማቴ16፡12፣ ማር8፡14-15፣ሉቃ12፡1፣ ሮሜ 6፡13-22፣ 1ቆሮ5፡6-8)። የጽድቅ የመጀመሪያ እርምጃ እና ከኃጢአት የመውጣትን ምሳሌ በሚያሳየው፣ በዚህ የቂጣ ሰንበት የመጀመሪያ ቀን(አቢብ15)በማክበረችን የምንደሰትበት ጊዜ ነው፣ ምክንያቱም በዚህ የሰንበት ቀን ሰባቱ የቂጣ ቀናት ይጀምራሉና። ሰባተኛው ወይም የመጨረሻው ቀን(አቢብ21)እንዲሁ ሰንበት ነው፣ይህም የዓለማዊ፣ የኃጢአት እና የዓመፅ መንገድ ትተን ፣የመድኃኒታችንን የያህሹዓ መሲሕን ጽድቅ ለመከተል መውጣትን ያያመለክታል (ዘጸ12፡15፣12፡20፣ዘኍ28፡17-25፣ሐዋ20፡6-7)። ወደ ኃጢአት ከሚመራው ከሐሰት ትምህርት ራሳችንን መጠበቅ እንዳለብን ለማስታወስ ለሰባት ቀናት ከቤቶቻችን እርሾ እናስወግዳለን፣ ምክንያቱም በድርጊት መንፈሳዊ ትምህርት ስለምንማረው ነው። ስለዚህ ለሰባት ቀናት እርሾ የለለውን ቂጣ እንበላለን፣ ይህም ሰንበቱን በቅንነትና በእውነት ማክበራችንን ያመለክታል(1ቆሮ5:7-8)።

10. የጴንጣቆስጤ ሰንበት(PENTECOST)

የጴነጣቆስጤ ቀን (ሽቮዝ) ሶስተኛ የዓመት ሰንበትና ልዩ ጉባኤ ቀን ነው(ዘሌ23፡15-21፣ ዘኍ28፡26)። ይህም ከቂጣ ሰንበት ቦኃላ ያሉትን 7 ሰንበት(ቅዳሜ)[49ቀን] ከቆጠርን ቦኃላ፣ቃጥሎ በለው በእሁድ ቀን(የመጀመርያ የሳምንቱ ቀን)(ስወን6)ለይ ይሆናል። ይህም ቀን ያህዌህ ከእስራኤል ልጆች ጋር፣ በሲና ተራራ ቃል ኪዳን የገባበት ቀን መታሰቢያ ሆኖ ይከበራል
(ዘጸ24፡4-8)።
እንድሁም ደግሞ ያህሹዓ በልዑል ሀይል ጉባኤውን (አማኞቹን) ለመሙላት ቃል የገባበት ቀን ነው(ሉቃ24፡49፣ ዮሐ14፡26፣15፡26 ፣ሐዋ1፡4-8)። ይህም የተፈጸመው በጴንጠቆስጤ ቀን፣ የያህዌም መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ምድር በተላከ ጊዜ ነበር (ዮሐ14:16፣ሐዋ2፡1-18)። ጴንጣቆስጤ ወይም የመጀመርያ ፍሬ ሰንበት የነፍሳት መከር መሰብሰብ የተጀመረበት ቀን ስሆን፣ ይህም ለያህዌ የበኩራት አይነት ነው(ሮሜ8፡23፣11፡16 ፣16፡5፣1ቆሮ15፡20-23፣16፡15፣ያዕ1፡18፣ ራዕ14፡4
)።

11.የመለከት ቀን(DAY OF TRUMPETS)

የጌታችን፤የያህሹዓ መሲሕን መመለስ በናፍቆት እንጠባበቀዋለን ምክንያቱም በመጨረሻው መለከት ድምፅ እና በመላእክት አለቃ ድምፅ ሲመለስ ዋጋችንን እንቀበላለን(1ቆሮ15፡22-23፣
15፡51-53፣1ተሰ4፡14-17፣ 1ጴጥ5፡4፣ ራዕ2፡23፣22፡12)። የመለከት ቀን አራተኛው አመታዊ ሰንበት ሲሆን ሰባተኛውም ወር ስጀምር(ኤታኒም1)ቅዱስ ጉባኤ ይሆናል(ሌዋ23፡24-25)። ጌታችን በመጨረሻው መለከት ስለመመለሱ ሐሴት እያረግን ልባችን በሰማያዊ ነገር ለይ እንድሆን ያሳስበናል(ሉቃ21፡27-28)። የመለከቱ መነፈት መልእክት እስራኤል እንድትሰበሰብ፣ ለጉዞ እንድትዘጋጅ፣ እና ለጦርነት እንድትነቀ የሚለውን ያስታውሰናል(ዘኍ10፡1-10)።

12.የሰርየት ቀን(DAY OF ATONEMENT)

የስርየት ቀን፣ ያህሹዓ ለኃጢአታችን ማስተሰረያ እርሱን መስዋዕት ማድረጉን ያመለክታል። በያህሹዓ በኩል ከታረቅን በኋላ፣ስለ ክቡር ሥራውም በደስታ እንመሰክራለን(ሮሜ5፡6-11፣2ቆሮ5፡18-21፣ ቆላ1፡19-22፣ ዕብ2፡18)። በሰበተኛ ወር በአስረኛው ቀን(ኤታኒም10) ለ24ሰዓት ምንም አንበላም እንጠጣምም(ሌዋ23፡32፣16፡29-31፣23፡27-32፣ ዘኁ29፡7)።ይህም እኛ ምን ያህል ሰውና ስጋዊ እንደሆንን እና የያህሹዓ የመስታረቅያ መስዋዕት እንደምያስፈልገን ያስታውሰናል። እንዲሁም የሰይጣንን መጥፋት(ዕብ2፡14)እና ዓለም ከያህሹዓና ከሰማይ አባታችን ጋር አንድ የምትሆንበትን በናፍቆት እንጠባበቃለን(ራዕ20፡1-3)። የስርየት ቀን የአመቱ 5ኛ ሰንበት ነዉ።

13.የዳስ ሰንበት (FEAST OF TABERNACLES)

የዳስ ሰንበት በቅርቡ የሚመጣውን የንጉሣችን ያህሹዓ የጽድቅ የአንድ ሺህ ዓመት ንግሥናን ያሳያል(ዘካ14፡16)። ያህሹዓ በያህዌህ ሕግ በሚገዛበት የሰላም፣ የብልጽግና እና የደስታ ጊዜ ይሆነናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ ማጥናታችን(2ጢሞ3፡14-17)እና በዳስ ሰንበት በፊቱ ለአምልኮ መምጣታችን ያህዌህ በመጨረሻ በምድር ሁሉ ላይ ስለምነግሰው፣በዚህም ለይ ያለን እምነታችንን ይመሰክራል። የያህዌህ ስም ባለበት ጉባኤ፣ የዳስ ሰንበት በሰባተኛው ወር ከ15ኛው ቀን ጀምሮ ለሰባት ቀናት(ከኤታኒም15-21)ይከበራል። የሰንበቱም የመጀመሪያ ቀን ስድስተኛው ዓመታዊ ሰንበት ነው(ሌዊ23፡34-36፣43፣ ዘኁ29፡12)።የሰንበቱም መጀመሪያና መጨረሻው ቀን የተቀደሰ ጉበኤ ስለሆነ የተግበር ስራ አይሰረባትም።

14.ስምንተኛው ቀን(THE EIGHTH DAY)

የስምንተኛው ቀን ሰንበት(ኤታኒም22) ሰባተኛው ዓመታዊ ሰንበት ነው(ሌዊ23፡36፣ዘኁ29፡35-36፣ነህ8፡18) ይህም ሰንበት ከያህሹዓ የሺህ አመት ግዛት በኋላ ያለውን የነጩን ዙፋን ፍርድ ጊዜ ያሳያል (ማቴ25፡32)። ስምንተኛው ቀን ክፉ ጠላት በእሳት ባሕር ውስጥ ከተጣለ በኋላ(ራዕ20፡10፣14፣15)ያለውን ዘለዓለማዊነትን ያመለክታል። ይህም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከያህዌህ ዘንድ ከሰማይ የምትወርድበት፣ ያህዌህ ራሱ ከሰዎች ጋር የሚቀመጥበት፣ሁሉም ነገር አዲስ የሚሆንበት፣የአዲስ የሰማይና ምድር ጊዜ ነው(ኢሳ66፡22፣ራዕ21፡1-5)። በስምንተኛው ቀን የተመሰለው የዘላለም ሕይወት፣የያህዌን ትእዛዛት ለሚጠብቁት ያህሹዓንም በማመን እስከ መጨረሻ ለሚጸኑት ቅዱሳን የሚሰጥ ነው(ራዕ14፡12፣ራዕ2፡7)

15.ወር መባቻ(NEW MOON)

የመጽሐፍ ቂዱስ ወራት የሚጀምሩት አዲስ ትንሽ ጨረቃ ስትወጣ (ስትታይ) ነው(2ነገ4፡23፣ ነህ10፡33፣ መዝ81፡3)።መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ወር መባቻ የሚጀመረው ለየንዳንዱ ወር አዲስ ጨረቃ በምትወጣበት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቀን የሚጀምረው እና የሚያበቃው በፀሐይ መጥለቂያ ነው(ሌዊ23፡32፣ መሳ14፡12፣18 ፣ማር1፡32)። ወር መባቻ በመንግስቱ ውስጥ ይጠበቃል(ኢሳ66፡23)።

16.ሐጥአት(SIN)

ሐጥአት የያህዌን ሕግ መተላለፍ(አመጸ)ነው(1ዮሐ3፡4)ስለዚህ ያለ ህግ ኃጢአት ሊኖር አይችልም(ሮሜ7፡6-12)። ሁሉም ሐጥአትን ሰርቶዋል የያህዌም ክብር ጎድላችዋል(ሮሜ3፡23፣ ዘጸ20፡1-20፣ ዘዳ5፡1-24)። የሐጥአት ቅጣት(ዋጋ)ሞት ነው(ዘፍ2፡16-17፣3፡19፣ሮሜ6፡23 ፣1ቆሮ15፡22፣ ዕብ9፡27)። ሞት እንቅልፍ እና ወደ አፈር መመለስ ነው(ዮሐ11፡11-14፣ መክ9፡5-6፣9፡10፣ኢሳ38፡18፣ መዝ115፡17)።

17.ቤዛነት (REDEMPTION)

ሁሉም ኃጢአትን ሰርተው የሞት ፍርድ ስላገኙ አሁን ንስሐ መግባት አስፈላጊ ነው; ይህ ማለት የያህዌን ቅዱስ ሕግ በመተላለፍ ላለፈው የሕይወት መንገድ መጸጸት እና አሁን ደግሞ የያህሹዓ አርአያነት ያለውን ሕይወት በመከተል ወደ መታዘዝ መንገድ መለወጥ ማለት ነው(ማቴ19፡17፣ዮሐ8፡11፣ዕብ6፡1፣9፡14)። ሞት ከሆነው ከህግ እርግማን ነፃ ለመውጣት ፣የግድ ያህሹዓ መሲሕ ለሐጥአታችን ሲል የከፈለውን መስዋዕት መቀበል ይኖርብናል(ማቴ26፡26-28፣ ቆላ3፡13፣ ዕብ9፡26፣10፡12፣ 1ጴጥ2፡21-24፣ 1ዮሐ1፡7-10)።ያህሹዓ ጠባቃችንና አስታራቅያችን ነው(1ጢሞ2፡3-5
)

18.ቅድስና (መቀደስ) (SANTIFICATION)

በያህሹዓ በማመን ከዓለም እርኩሰት ከተለዩ በኃላ፣ ውስጣዊና ውጪያዊ ቅድስና መጠበቅ ግዴታ እንደሆነ እናምናለን። ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ ነውና፣ በዘሌዋውያን 11 እና ዘዳግም 14 ላይ ያለውን የንፁህ ምግብ መብላትን ህግ እንጠብቃለን። ይህም በመታጠብና ባለመታጠብ እንድሁም በመቀደስና ባለመቀደስ መካከል ያለውን ልዩነት ያስተምረናል(2ቆሮ6፡16-18)። እኛ የሐሳባችን ውጤት ነንና የአዕምሮአችን ትኩርት የሚወስዱ ነገሮች፦ እንደ ማንበብ፣ የTV ፕሮግራሞች፣ ራድዮ፣ ጎአደኛ እና ተባባርያችንን መምረጥ አለብን። ምክንያቱም በያህዌ ፊት መቀደስ ያስፈልጋልና፣ የምንበላው ንጽሁ፣ የምናስበው ንጸሁ፣ የምንኖረው ኑሮ ንጽሁ መሆን አለበት። በዓለም ላሉት ምሳሌ ልንሆን ይገባናልና(1ጢሞ3፡7)፣በያህዌ ፊት ስንመላለስ በቅድስና መላለስ አለብን(ማቴ5፡48፣1ቆሮ3፡17፣1ጴጥ15-16፣ራዕ21፡27)
።

19.ቅባት(ANOINTING)

የያህሹዓ ፍጹም መስዋዕት ከሕመማችን እንድንፈወስ አስችሎናል(ኢሳ53፡3፣ያዕ5፡13-20)። የማሕበሩ ሽማግሌዎች የታመመውን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።ምክንያቱም ሕመመችን መፈወስ የሚችለው፦በመጀመሪያ በጸሎት ወደ ያህዌህ በመመለስ፣በእርሱ እና በእሱ ምህረት በመታመን ነው።

20.አስራት(TITHING)
ያህዌህን በንብረታችን ማክበር መቻል መታደል ነው(ምሳ3:9)እንድሁም የያህዌህን ሥራ በአስራትና በመባችን ለመደገፍ የምናቀርበው ነገር ሁሉ የአምልኮ ተግባር ነው(ሌዊ27፡30-33፣ ሚል3፡8-12፣ማቴ23፡23፣1ቆሮ9፡1-25፣2ቆሮ9፡1-15)። አስራት ከአስር አንድ እጅ(1/10) ለያህዌ ማለት ነው።ሌላ ደግሞ ያህዌ በጥበቡ ሁለተኛ አስራት የሰንበቶቹን ቀናት እንድንሳተፍ እና መደሰት እንድንችል ሰጥቶናል(ዘዳ14፡27-29፣26፡12-17)። መስጠት ከመቀበል የበለጠ መቀዳስ ነውና ስንሰጥ በደስታ እንስጥ። ያህዌ ለጋሽ እንደ ሆነ ማወቅና ለምያስፈልገን ነገር ሁሉ እንደሚያስብልን መረዳት አለብን።

21.ጠላት(THE ADVERSERY)
ሰይጣን መንፈስ ነው፣ በመጀመሪያ ሉሲፈር የሚባል የተቀባ ኪሩብ ነበር። እራሱን ከፍ ከፍ አደረገ ከሰማይም ተጣለ(ኢሳ14፡12-20፣ ሕዝ28፡13-19፣ ሉቃ10፡18፣ ረዕ12፡7-9)።ዲያብሎስ የያህዌ ሕዝብ ጠላት ስለሆነ(ዮሐ8፡44፤ ራዕ12:10)፣በመጨረሻ ይጠፋል(ኢሳ14፡18-19፣ሕዝ28፡16፣ ሮሜ16፡20፣ ዕብ2፡14)። ሰይጣን የያህዌን መንግሥት መቋቋምን ለማደናቀፍ እየሞከረ ነው(ማቴ4፡1-11)። በያህዌህ እርዳታ ዲያብሎስን መቃወም እንችላለን ከእኛም ይሸሻል(ያዕ4፡7)

22.ሟችነት(MORTALITY)
ሙታን በመቃበራቸው የማያስቡ ሆነው በሞት እንቅልፍ እስከ ትነሳኤ ሙታን ድረስ ይቆያሉ። (እዮ14፡12-14፣ዳን12፡2፣ዮሐ5፡29፣1ቆሮ15፡51-56፣1ተሰ4፡13-17፣ዕብ11፡13፣11፡39)። ያለመሞትን ሁላችንም የምንፈልገው ነገር ነው(ሮሜ2፡7፣1ቆሮ15፡53-54)ይህም በያህሹዓ መስሒ በኩል ቀርቧል(ዮሐ3፡15፣17፡23 ፣2ጢሞ1፡10)። የማይሞት ያህዌ ብቻ ነውና፣ (1ጢሞ1፡17፣6፡16)። ሰው የማይሞት ነፍስ የለውም(መዝ6፡5፣115፡17፣ ኢሳ26፡19)። ነገር ግን ነፍሳት ሊሞቱ ይችላሉ(ሕዝ18፡4፣18፡20፣10፡28)።ሰው እራሱ ህያው ነፍስ ነው!

23.የአማኞች አካል(THE BODY OF BELIVERS)
ያህሹዓ መሲህ የአካሉ/የኤክሌሲያ/የጉባኤው/የማህበሩ መሰረት እና የማዕዘን ድንጋይ ስሆን ይህ የተጠሩ የአማኞች አካል ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ2 ጀምሮ የተወደደውን የጌታችንን መስዋዕትነት የተቀበሉ እና ሕይወታቸውን እንደ ያህዌህ ቃል የቀየሩ አማኞች ናቻው(ማቴ12፡50)። በዚህ በአማኞች አካል አማካኝነት ለሚመጣው መንግሥት ሥልጠናና ዝግጅት እየተካሄደ ነው(1ጴጥ2፡9-10፣2፡5፣ ራዕ1፡6፣20፡6)። የጸጋውም ስጦታዎች በኤክሌሲያ(በማህበሩ) ውስጥ የሚሰጡት፡- ቅዱሳንን ለመብቃት፣ ለአገልግሎትና የመሲሑን አካል ለማነጽ ነው(ኤፌ4፡7-13፣1ቆሮ12፡7-10፣12፡28-30)። ማህበሩ መንፈሳዊ ፍሬዎች(ገላ5፡22-23) የሚገለጡበት ቦታ ስሆን ፣ከመሲህ ማህበር ጋር ያለን ግንኙነትና ከያህሹዓ ጋር ያለን ግንኙነት አንድ መሆን አለበት(ማቴ12፡50፣23፡40)። ከሐዋርያው ጳውሎስ ዘመን ጀምሮ በነበረው በመጀመሪይቱ ማህበር(ጉበኤ) ስርዓት መሠረት፣ የጉባኤው እህቶች በአምልኮና በጸሎት ጊዜ ራሳቸውን መሸፈን አለባቸው። ጳውሎስ ለዚህ ስርዓት ያለውን ምክንያት በ1ኛ ቆሮንቶስ11፡1-16 ጠቅሷል። ያህዌህ ፣ያህሹዓንም ጨምሮ የሁሉ ራስ ነው። አሁን ሊቀ ካህናችን ያህሹዓ ነው እና በምሳሌያዊ ሁኔታ የዚያን የአገልግሎት መጠምጠሚያውን ለብሷል(ዘሌ21፡10)። በምድር ላይ ወንድ የያህዌ ክብር ምሳሌ ስለሆነ እርሱን ሰይሸፍን በፊቱ ይቆማል። በሌላ በኩል ሴት የወንድ ክብር ስለሆነች እርሷን መሸፈን አለባት። ወንድ የሴት ራስ እንደሆነ ያህሹዓም የማሕበሩ ራስ ነው፣ ስለዚህ ያህሹዓ የማሕበሩን እንደወደደ፣ በል ምስቱን መውደድ አለበት (ኤፌ5:23-25
)
::

24.ፍቅር (love)
በምናስተምረው ትምህርትና በለን እምነት ምሳሌ መሆን አለብን። ያህሹዓን በፍቅር፣ በቅንነት፣ በትህትና፣ በእምነት፣ በተስፋ፣ በትዕግስት እና በአክብሮት ለመምሰል እንጥራለን(ሌዊ19፡17-18 ማቴ(መዕራፍ5፣6፣7)፣ማቴ22፡39፣1ቆሮ6፡1-11፣1ጴጥ2፡21-23)። ፍቅር በቤታችን፣ በማህበረሰባችንና በማህበራችን ውስጥ ለመጠበቅ የምንጥር ቁልፍ ባህሪ ነው። ፍቅር ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ለሌሎች ማሰብ ነው።ፍቅር እውነተኛ የያህዌ ህዝብ ምልክት ስለሆነ ወንድማማቾች ባሉበት ሁሉ መታየት አለበት። መዳን ለሰው ልጆች ሁሉ በነጻ እንደሚሰጥ እናምናለን። ያህዌ የአሕዛብ ሁሉ ፈጣሪ ነው እና ቤቱንም ለሰዎች ሁሉ የጸሎት ቤት አደረገው(ኢሳ56፡7፣ሐዋ8፡27-39፣ገላ3፡28፣ቆላ3፡11)። የያህዌ ፍቅር በልጁ በያህሹዓ መስሒ መስዋዕት ለሚያምን ሁሉ የተገለፀ ነው(ራዕ3፡20፣22፡17)። ትእዛዛቱን ሁሉ በማክበር ለእርሱ ያለንን ፍቅር እናሳያለን(1ዮሐ2፡5፣5፡3፣ 2ዮሐ1፡6
)።

25.ለአባልነት መመዘኛዎች(QUALIFICATION FOR MEMEBERSHIP)
ንስሃ መግባት፣ በያህሹዓ ስም መጠመቅ እና መንፈስ ቅዱስን መቀበል የመሲሁ አካል አባል ለመሆን የሚጠበቁ እርምጃዎች ናቸው(ሐዋ2፡38)። በእውቀትና ያህሹዓ ጸጋ የማደግ ሕይወት፣ እያንዳንዱም በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሱን መዳን መስራት እና ለሕግ መታዘዝ ከሁሉም የሚጠበቅ እውነተኛ መለወጥን የሚያሳዩ ናቸው(ፍል2፡12፣ኤፌ4፡13)።
የያህሹዓ መስሒ እረምጃ መከተል አለብን ፤ጺም ማሳደግንም ጨምሮ (ነገር ግን ጺም ማሳደግ የግል ምረጫ ነው)።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያመለክተው ጌታችን ያህሹዓ መስሒ ጺም እንዳሳደገ ነው(ኢሳ50፡6)። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያመለክቱት እስራኤላዊያን ጺም ማሳደግ እንደአለባቸው ነው(ሌዋ14፡9፣13፡29-30)፣ ነገር ግን ቅርጽ (point) መሆን የለባትም(ሌዊ19፡27፣21፡5)።
➻እያንዳንዱ የማሕበሩ አባል ይህንን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሆነ በደንብ ይረዳው።

፨በያህሹዓ የሆነ የያህዌ ጉባኤ፣ ብዙ መፅሔቶችን አሳትሟል
➻የኢትዮጵያ አድራሻ፦
09 11 78 25 46
/09 30 88 03 65

➻ዓለማቀፍ አድራሽ፦
©YAHWEH'S ASSEMBLY IN YAHSHUA
2963 COUNTY ROAD 233
KINGDOM CITY, MISSOURI 65262
ONLINE AT:- WWW. YAIY.ORG
CALL TOLL FREE (877) 642-4101
MAIN LINE :-(573)642- 4100